

# መራሂት

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ሴት ብልህ ናት። ሴት ቆራጥ ናት። ሴት አርቆ አሳቢ ናት። ሴት ፍቅር ናት። ሴት ጥበብ ናት። ሴት ብቁ አሰተዳዳሪ ናት። ሴት እናት ናት።

ሴት እሩህሩህ ናት ሴት አዛኝ ናት። ሴት ለራህብ ደራሽ ናት። ሴት ጭንቅን ተጋሪ ናት። ሴት አጽናኝ ናት። ርህርትት

ሴት ብሩህ ናት። ሴት ሚሰጢር ናት። ሴት ጀግና ናት። ሴት እውነት ናት። ሴት ማህበራዊት ናት።

ሴት ከእናትነት ፀጋዋ ጋር ሰፊ የሆነ መክሊተ ፀጋ በፈጠራት አምላክ ተሰጥቷታል። እኔ በግሌ ቀደም ባለው ጊዜ በዜና ስከታተል ከነበረኝ አክብሮት ይለቅ በአካል ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር ሳይ ከላይ የዘረዘርኳቸውን ጥልቅ ፆታዊ በረከት ተጎናጽፈው ነበር ያገኘኋቸው።

ይህን አንዲት እህቴ እንዲህ ነበር የገለፀቸው .....
„ከቶ ምን እዬበላሽ ይሆን ይህን ሁሉ ጥንካሬ ያገኘሽው“

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ህዳር 23 ቀን 2008 ጄኔቫ ሲዊዘርላንድ ስብሰባ ላይ ....

„ዘመን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል“ እንዲሉ ...
ያን የመሰለ ለዛ አና ውበት የተጎናፀፉትን መራሂተ እኩልነት፤ ብቃተ መሰታውትን ወያኔ ቀራኒዎ አዋለ። ጨለማ በዬነ። ፋሽስትነት ማለት ከዚህ በላይ ምንድን ሊገልጠው ይችል ይሆን?

ያን ማይጠገብ አንደበት በሰንሰለት ... ያን የመረሂነት ብቃት በተስፋ መጠት ጉድጓድ
ያን የመሰለ የቁርጠኝነት ትህትናዊ ሰላማዊ ጉዞ እንቅፋት ፈጠረለት ...
ነጎድጓዳማው በረዶ በተውልዶ ተሰፋ ላይ ማቱን አወረደ ......

በምንም ዓይነት መሰፈርት ክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር የተሰጣቸውን ስልታዊ የመሪነት ጥበበ ብልሃት የሚመዝን በዚህ ዕድሜ አንስት ለእኔ ህሊና አላገኘሁለትም። ድንቅ መረሂተ ቀንዲል ናቸው!!!

በወጣትንት፤ በአፍላነት እንደ ጎልማሳ፤ እንደ ሃይኖት ትክክለኛ አባቶች። ሽበታቸው በውስጣቸው እንደበቀለው አዛውንታት በመቻቻል በማስማማት በማለስለስ ለህግ የበላይነት ታግሎ ማታገልን የታደሉ ብልህ ሴት ....

ሴቶች በእውን የምንለብሰው፣ የምንጫማው፣ የምንተኛበት፣ የምንጓዝበት፣ ደላን ይሆን አካላችን እግር ብርት ሆነው።

አንዲት ልጃቸው እና ደካማ እናታቸውን ለበላሃሰቦች ትተው ለእኛ እንዲህ ሲንገበገቡ ሲገፈተሩ፣ ሲገፉ፣ ሲለበለቡ በግለምጫ ሲወቁ እጃችን አጣምረን እንቀመጥ ወይንስ አጋራነታችን በተግባር እናስጊጥ ... የቱ ይሆን ምርጫችን?!

የማከብራችሁ እህቶቼ ....

በእውነት እንቁረጥ በሁሉም መስክ ተግተን እንታገል። ቀዳሚ ዋስ ጠበቃ ለመሆን የፊት ረድፈኛ እንሁን እባካችሁን!?

እራሳችን በማስተወል ሆነን አንጠይቅ አዎ እኒያ ፍልቅልቅ ... ጨለማ ውስጥ ... ዳፍንት ውስጥ በጨካኞች እጅ ነገ ምን ያደርጓቸው ይሆን ... ነፍሳችን እናባትላት። ሌሎችም እስር ላይ ላሉ እህቶቻችንም ....

ሩሃችነን ፋታ አሳጥተን በተግባራዊ ተሳትፎ እንተጋ ዘንድ ለህሊናችን እንፍቀድለት። እንዲጠይቀን እንዲያፈጥጠን። የክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የክፉ ቀናቸው ዋቢ እንሁን።

የፆታ ፀጋችንን ለፀረ ወያኔ ትግል እናውለው።
ፅናትን የመገበን ወርቅ ይደምቃል እንጂ አይወይብም!!
እንጽና!